# የአኩሪ አተርን ምርታማነትና ጥራት ለመጨመር የሚያስችሉ 16 የአሰራር ሂደቶች





## ምስጋና

የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራም ይህንን የአኩሪ አተር አመራረት መመሪያ ለማዘጋጀት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት በተለይም ቴክኖሎጅዎችን፣ መረጃዎችንና ፎቶዎችን በነፃ እንድንጠቀም ላደረጉ አካላት በሙሉ ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል፡፡ በተለይም የፓዌ ግብርና ምርምር ማዕከል የተለያዩ የአኩሪ አተር ቴክኖሎጂዎችን በማመንጨትና በማስተዋወቅ ረገድ ላደረገው አስተዋጽኦ የላቀ ምስጋና ይገባዋል፡፡

**ማውጫ** **ገጽ**


መግቢያ ........................................I

1. የማሳ ዝግጅት........................................1
2. ዝርያ አመራረጥ........................................2
3. ሰብል ማፈራረቅ........................................3
4. የዘር ዝግጅትና መጠን........................................4
5. የዘር ወቅት........................................5
6. የአዘራር ዘዴ........................................6
7. የማዳበሪያ ዓይነት፣ መጠንና አጠቃቀም..7
8. ማጣቀስ ወይም መቀነስ........................................8
9. አረምን መከላከል........................................9
10. ነፍሳት ተባይን መለየትና መከላከል ...10
11. በሽታን መለየትና መከላከል................14
12. ማጨድና ማድረቅ........................................17
13. መውቃትና ማበጠር........................................18
14. ማዳበሪያ/ጆንያ አመራረጥና አያያዝ.....21
15. ማጓጓዝ ........................................22
16. ክምችት........................................23

ምግብ ዝግጅት........................................24

# መግቢያ

## የአኩሪ አተር ጥቅም

አኩሪ አተር በዓለም ላይ በስፋት የሚመረት ዘርፈ-ብዙ ጥቅም ያለው ሰብል ነው፡፡ ከምግብነት ባሻገር የእንስሳት መኖ፣ ቅባትና ነዳጅ ለማምረት ያገለግላል፡፡ ከፍሬው ይዘት ከ80% በላዩ ለሰውና ለእንስሳት ምግብነት የሚውል ሲሆን ከ18 እስከ 20% የሚሆነው ደግሞ ዘይት ነው፡፡

- አኩሪ አተር ከ38% በላይ ፕሮቲን አለው፡፡
- በስብና በሚኒራሎች የበለፀገ ነው፡፡
- ከዱቄቱ ወተትና አይብን ጨምሮ የተለያዩ ምግቦችን ለማዘጋጀት ያገለግላል፡፡
- ዘይቱ ለዳቦ መጋገሪያ፣ ለጥብሳ ጥብስና የገበታ ቅቤ መስሪያ፤ ለሰላጣ ማጣፈጫነት እና ሰርዲን ለማዘጋጀት ይጠቅማል፡፡
- ፋጉሎው ለዶሮና ለተለያዩ የቤት እንስሳት መኖ ማቀነባበሪያነት ይጠቅማል፡፡
- በማሳ ላይ የሚቀረው ተረፈ ምርት ለእንስሳት መኖነትና ለኮምፖስት መስሪያ ያገለግላል፡፡
- አኩሪ አተር ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነትም ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ፡-
  - የተፈጥሮ ነዳጅ ይወጣበታል፤
  - በተፈጥሮ የሙቀት ምንጭነት ያገለግላል
  - ከዘይቱ ቀለም፣ የተለያዩ የፕላስቲክ ውጤቶችና የፅዳት ዕቃዎች ይፈበረካሉ፤
  - ሙጫ፣ የወለል ንጣፍ፣ ቺፕውድና ፋይዜት ይሰራበታል፤
  - ለመፃፊያ ቀለም፣ ለመኪና ውስጥ ንጣፎችና ለመሳሰሉት የፋብሪካ ውጤቶች መስሪያ ይጠቅማል፡፡

# 1 የማሳ ዝግጅት



## ለአኩሪ አተር የሚመረጠው ማሳ፡-

- በጣም ተዳፋት ያልሆነ፤ የተንጣፈፈና ለም አፈር ያለው ቢሆን ይመረጣል፤
- ጥቁር ኮትቻ፣ ረግረጋማ ወይንም በጣም አሸዋማ አፈር አይመቸውም፡፡

## የማሳ ዝግጅት፡-

- ማሳውን በደንብ ማፅዳት እና ከሁለት እስከ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ በማረስ አፈሩን በማለስለስ ለዘር ዝግጁ ማድረግ

## 2 ዝርያ አመራረጥ



- ዝርያን ለመምረጥ የአካባቢውን የዝናብ መጠን ማወቅና ዝርያው ከአካባቢው ጋር የተላመደ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- ለዝናብ አጠር/ቆላማና ከ460-700 ሚ.ሜ ዝናብ ለሚያገኙ አካባቢዎች ከ100 ቀን በታች የሚደርሱ ዝርያዎችን (ኖቫ፣ አዋሳ-95፣ ኒያላ፣ ዊልያምስ፣ ክራውፎርድ ወይም አዋሳ-04ን) መዝራት፣
- መካከለኛ የዝናብ ስርጭት (ከ700-1000 ሚ.ሜ) ለሚያገኙ አካባቢዎች ከ100-120 ቀናት ባለው ጊዜ የሚደርሱ ዝርያዎችን (ጊሻም፣ ግዞ፣ አፍጋት፣ ክላርክ-63ኬ፣ ኮከር-240 ወይም ኒያላን) መጠቀም
- ከፍተኛ ዝናብ (ከ1000 ሚ.ሜ በላይ) ላላቸው አካባቢዎች ከ120 ቀን በኃላ የሚደርሱ ዝርያዎችን እንደ በለሳ-95፣ ወጋየን፣ ኢትዮ-ዩጎዝላቪያ የመሳሰሉትን መጠቀም ይመከራል፡፡

# 3 ሰብል ማፈራረቅ

## ከአኩሪ አተር ጋር ሊፈራረቁ የሚችሉ ሰብሎች



ማሾ



ሰሊጥ



ጥጥ



ማሽላ

- አንድን ሰብል በአንድ ማሳ ላይ ከ2 ዓመት በላይ አለማምረት
- ከሰሊጥ፣ ማሽላ፣ ጥጥ፣ በቆሎ፣ ማሾ ጋር ማፈራረቅ፣

## የሰብል ማፈራረቅ ጥቅም:-

- የመሬት ለምነትን ያሻሽላል
- የተባይና በሽታ ጥቃትን ይቀንሳል
- የቤተሰብ የምግብ ዋስትናን ያረጋግጣል
- የአርሶ አደሩን ገቢ ይጨምራል

# 4 የዘር ዝግጅትና መጠን

## የዘር ዝግጅት

- ዝርያውና የዘር ምንጩ የታወቀ፤
- የዘር መጠኑና ቀለሙ ተመሳሳይ የሆነ፤
- ጥራቱ 99% እና የብቅለት መጠኑ ከ85% በላይ የሆነ ዘር መጠቀም ይመከራል
- ከመዘራቱ በፊት በህያው ማዳበሪያ መለወስ ወይም ማከም፤
- የታከመውን ዘር በ24 ሰዓት ውስጥ መዝራት፡፡



ተበጥሮ ለመዘራት የተዘጋጀ የአኩሪ አተር ዘር

## የዘር መጠን

- የዘር መጠኑ እንደ ዝርያው የሚለያይ ቢሆንም ከ60 - 80 ኪ.ግ ዘር በሄክታር ያስፈልጋል፡፡

# 5 የዘር ወቅት






- አኩሪ አተር ከሰኔ አጋማሽ እስከ ሐምሌ መጀመሪያ ሳምንት ተዘርቶ ማለቅ አለበት አፈሩ በቂ እርጥበት ሲይዝና ለዘር ብቅለት በቂ መሆኑን አረጋግጦ መዝራት
- ከ100 ቀን በታች የሚወስዱ ዝርያዎችን ሐምሌ መጀመሪያ ላይ መዝራት
- ለመድረስ ከ100 ቀን በላይ የሚወስዱ ዝርያዎችን ሰኔ ውስጥ መዝራት ይመከራል፡፡

## 6 የአዘራር ዘዴ

### አኩሪ አተርን በመስመር መዝራት ይመከራል



አኩሪ አተር በመስመር ሲዘራ

በሁለት መስመሮች መካከል የሚኖረው ርቀት እንደዝርያው የመድረሻ ጊዜና ቅርንጫፍ የማውጣት አቅም ይለያያል፡፡

- ፈጥነው ለሚደርሱ ዝርያዎች
    - በመስመር መካከል 40 ሳንቲ ሜትር
    - በተክሎች መካከል ከ3 እስከ 5 ሳንቲ ሜትር መሆን አለበት፡፡
- ለአጨዳ ከ100 ቀን በላይ ለሚያስፈልጋቸው ዝርያዎች
    - በሁለት መስመሮች መካከል 60 ሳንቲ ሜትር እና
    - በተክሎች መካከል ከ3 እስከ 5 ሳንቲ ሜትር አራርቆ መዝራት ያስፈልጋል

### የዘር ጥልቀት

- ከ5 ሳንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም

# 7 የማዳበሪያ ዓይነት፣መጠንና አጠቃቀም



ኤን ፒ ኤስ የአፈር ማዳበሪያ

ለአኩሪ አተር ሰው ሰራሽ፣ የተፈጥሮ ወይንም ህያው ማዳበሪያ መጠቀም ይቻላል፡፡

## ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ

- በዘር ወቅት 50 ኪ.ግ ኤን.ፒ.ኤስ ወይም 100 ኪ.ግ ዳፕ በሄ/ር ዘሩ በሚጣልበት ቦይ ውስጥ መጨመርና አፈር በስሱ ማልበስ፣

## የተፈጥሮ ማዳበሪያ

- ከ200 እስከ 300 ኪ.ግ. ፍግና ብስባሽ በሄክታር መጠቀም

## ህያው ማዳበሪያ (ራይዞቢዩም ባክቴሪያ)

- 500 ግራም ህያው ማዳበሪያ ለአንድ ሄ/ር ከተዘጋጀው ዘር ጋር ማሸትና መዝራት፣
- ህያው ማዳበሪያን መጠቀም ምርትን በ86% ይጨምራል፡፡

## የተመረጡ የህያው ማዳበሪያ ዓይነቶች

- ማር-1495 ለመተከል አካባቢ
- ሌግዩም-ፊክስ ለጅማና አካባቢው
- ኤስ ቢ-12 ለታች አርማጭሆ እና መተማ አካባቢ መጠቀም፡፡

# 8 ማጣቀስ ወይንም መቀነስ



ቡቃያ ባልበቀለበት ባዶ ቦታ ላይ እንደገና መዝራት ማጣቀስ ሲሆን የበዛውን ተክል ማሳሳት ቅናሶ ይባላል፡፡

## ማጣቀስ

- ከሳምንት በኋላ ዘሩ በሁሉም መስመሮች ላይ በሙሉ መብቀሉንና ክፍት ቦታ አለመኖሩን መከታተል፤
- በመስመሩ ውስጥ ቡቃያ የሌለበት ባዶ ቦታ ከታዬ ሰብሉ ብቅለቱን እንደጨረሰ እንደገና እርጥበት ባለበት ጊዜ ዘር መዝራት/ማጣቀስ ያስፈልጋል፡፡

## መቀነስ

- ቡቃያ የበዛበት ቦታ ካለ በየ5 ሳንቲ ሜትር (በአውራጣት ልክ) አንድ ተክል በመተው ማሳሳት፤
- ጠንካራውን ተክል በመተው ደቃቃውን ቀስ ብሎ መንቀል ወይንም ከአንገቱ ላይ መቀንጠስ፤
- ስንነቅል የቀረው ተክል ሥር እንዳይጎዳ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# 9 አረምን መከላከል

አኩሪ አተርን የሳር ዘርና ቅጠለ-ሰፊ አረሞች ሊያጠቁት ይችላሉ፡፡ አረም፡-

- ንጥረ-ነገርን፣ ውኃንና የፀሐይ ብርሃንን ይሻማል
- ሰብሉን ያቀጭጫል
- አጨዳን ያውካል
- የምርት ጥራትን ይቀንሳል፡፡

አኩሪ አተር በወቅቱ ካልታረመ ምርታማነቱ ከ60% በላይ ሊቀንስ ይችላል፡፡

## በእጅ ማረም

1ኛ አረም ሰብሉ ከበቀለ ከ2ኛው እስከ 3ኛው ሳምንት፣
2ኛ አረም ከ5ኛው እስከ 6ኛው ሳምንት፣
3ኛ አረም እንዳስፈላጊነቱ መታረም አለበት፡፡

## በፀረ-አረም መርዝ መከላከል

- ዱዋል ጎልድ አንድ ሊትር፣ ኮዳል ጎልድ 2.5 ሊትር፤ ፔንድመንታሊን 1.5 ሊትር በሄ/ር በ200 ሊትር ውሃ በጥብጦ ሰብሉ ከተዘራ ከአንድ ቀን በኃላ እርጥበት ባለው አፈር ላይ መርጨት፤

## በእጅና በፀረ-አረም መርዝ መከላከል

- ፀረ-አረም መርዝ ተረጭቶ የአረም ቁጥጥሩ አጥጋቢ ካልሆነ አንድ ጊዜ በእጅ ማረም ወይም ፀረ-አረሙን ደግሞ መርጨት፡፡ ሆኖም ግን ሰብሉን እንዳይጎዳው መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡



# 10 ነፍሳት ተባይን መለየትና መከላከል

## ነፍሳት ተባይን መለየት

የአኩሪ አተርን ቅጠል የተለያዩ ጢንዚዛዎች፣ ተምችና ሰንዛሪ ትሎች ይበሉታል። ግንዱን ግንደ ሰርስር እና የቦለቄ ዝንብ፣ ስሩን ስር ቆራጭና ስር ቦርቧሪ ትሎች፣ ቆባውን ደግሞ የሚበሱ ትሎች ያጠቁታል። እነዚህም ከዚህ በታች በስዕል ተመልክተዋል።




የጢንዚዛ ጥቃት



የጓይ ትል



ሰንዛሪ ትል



ተምች



ነጭ ዝንብ



ቀይ ቅንቅን



ክሽክሽ



ምስጥ (ንግስትና ሠራተኛ)





የሽንኩርት አንጥረኛ/ ጎልምስና እጭ



የቦለቄ አንጥረኛ

# ነፍሳት ተባይን መከላከል

## በባሕላዊ ዘዴ መከላከል

- ሰብል ማፈራረቅ፣
- ንፁህ ዘር መጠቀም፣
- ደጋግሞ ማረስ፣
- ወቅትን ጠብቆ መዝራት፣
- ተባይን የሚቋቋሙ ዝርያዎችን መጠቀም፣
- ምስጥን ለመከላከል ኩይሳውን በማፍረስ ንግስቲቱን መግደል ወይም ኩይሳውን በጢስ ማጠን

## በፀረ-ተባይ መርዝ መከላከል

## ዘሩን በመርዝ ማሸት

- 350 ሚሊ ሊትር ክሩዘር 350 ኤፍ.ኤስ ከ100 ኪ.ግ ዘር ጋር ማሸትና ወዲያውኑ መዝራት



## የመስክ ርጭት

ነጭ ዝንብ፣ ክሽክሽ፣ ቅንቅን፣ አንጥረኛ፣ ጓይ ትልና ተምችን የመሳሰሉ ተባዮች መስክ ላይ ሲከሰቱ ከሚከተሉት ፀረ-ተባይ መርዞች አንዱን መርጦ ለአንድ ሄክታር ማሳ በ200 ሊትር ውሃ በጥብጦ መርጨት:-

- ካራቴ 5% ኢ.ሲ ከ1.5 እስከ 2 ሊትር
- ዳይሜቶኤት/ሮገር 40% ኢ.ሲ. ከ1.5 እስከ 2 ሊትር፣
- ዲያዚኖን 60% ኢ.ሲ. ከ2 እስከ 3 ሊትር
- ፋስታክ 2.5% ኢ.ሲ. ከ2 እስከ 3 ሊትር
- ማላታዮን 50% ኢ.ሲ. 2 ሊትር በሄ/ር መጠቀም፡፡

## ምስጥን ለመከላከል፡-

- ዲያዚኖን (ዱርስባን) ከ2.5 እስከ 3 ሊትር
- ፓይረኒክስ 3 ሊትር በሄ/ር ከ200-300 ሊትር ውሃ በጥብጦ ኩይሳው ውስጥ መጨመር ወይም ማሳው ላይ በቂ እርጥበት ባለበት ጊዜ መርጨት፡፡

## ለቅጠል-በል ተባዮች (ለምሳሌ ወርቂት)

- ዲያዚኖን 60% ኢ.ሲ. ከ2 እስከ 3 ሊትር
- ማላታዮን 50% ኢ.ሲ. በሄክታር 2 ሊትር መጠቀም፡፡

# 11 በሽታን መለየትና መከላከል

**በሽታን መለየት:-** የበሽታውን አይነት ለመለየት ምልክቱን በደንብ መመልከት ይገባል።



ቡናማ ጠቃጠቆ



ቡናማ ጠባሳ



የገንፎ ዓይን ጠባሳ



ደቃቅ ጠቃጠቆ



ዋግ



ግንድ አድርቅ



የሥር አመዳይ



ዱቄታማው አመዳይ



ነጭ ሻጋታ



የሞዛይክ ቫይረስ ጥቃት

# በሽታን መከላከል

## ባህላዊ የበሽታ መከላከያ ዘዴ

- በሽታ የሚቋቋሙ ዝርያዎችን መዝራት፤
- ሰብልን ማፈራረቅ (ከ2 ጊዜ በላይ በአንድ ማሳ ላይ አለመዝራት)
- የሰብሉን ቅሪት ከማሳ ማስወገድ ወይም መቅበር፤

## ዘሩን በፀረ-ሻጋታ መርዝ መለወስ

- 350 ግራም ክሩዘር ለአንድ ኩንታል ዘር መለወሻ መጠቀም

## ማሳ ላይ በሽታ ሲከሰት ፀረ-ሻጋታ መርዝ መርጨት

- ለዋግ፣ ሴፕቶሪያ፣ አመዳይ፣ የገንፎ ጠቃጠቆ፣ ጠባሳዎች፣ አመዳይ እና አንትራክኖስ ሰብሉ በሚያብበበት ወቅት፤
- ሪዶሚል 1.5 ኪ.ግ ወይንም ኮሳይድ 2 ኪ.ግ በሄ/ር፤
- ለምች ክሩዜት 2 ኪ.ግ በሄ/ር ከ200-300 ሊትር ውኃ በጥብጦ መርጨት፤

# 12 ማጨድና ማድረቅ



## ማጨድ

ሰብሉ ለአጨዳ መድረሱን የሚያሳዩ ምልክቶች፡

- ከ90% በላይ ቅጠሉ ይረግፋል
- ፍሬውን ፈልፍለው በጥርስ ሲሞክሩት በቀላሉ አይጨፈለቅም
- ቆባውን ሲያወዛውዙት የሚንኮሻኮሽ ድምጽ ያሰማል

## ማድረቅ

- የታጨደውን ሰብል በደረቅና ፀሐይ በሚያገኘው ቦታ በመከመር እስከ 15 ቀን ማድረቅ

# 13 መውቃትና ማበጠር

## መውቃት

አኩሪ አተር በሰው፣ በእንስሳ ወይንም በመውቂያ መሳሪያ ሊወቃ ይችላል።



አኩሪ አተር በእጅ ሲወቃ



አኩሪ አተር በመውቂያ መሳሪያ ሲወቃ

- ለመውቃት መድረሱን ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱ ቆምባው በእጅ ሲታሽ በቀላሉ መሰባበሩ ነው፡፡
- በደረቀው ሰብል ላይ ዝናብ ከጣለ ከመወቃቱ በፊት እንደገና ማድረቅ እና የእርጥበት መጠኑ ከ13% በታች መሆኑን ማረጋገጥ፤
- አውድማውን በንፅሕና ማዘጋጀት፤
- ሲወቃ ዘሩ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት መጠንቀቅ
- በመውቂያ መሳሪያ ከሆነ መሳሪያው ፍሬውን የማይሰባብረው መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ከአንድ በላይ ዝርያ የሚያመርቱ ከሆነ የመውቂያ ቦታውን መለየት ወይንም በተለያየ ጊዜ አውድማውን በደንብ ካፀዱ በኋላ መውቃት ያስፈልጋል፡፡
- በትላልቅ እርሻዎች ትራክተር ወይም ፒክ-አፕ መኪና በላዩ ላይ በመንዳት መውቃት ይቻላል፡፡

# ማበጠር



በመንሽ ሲነፋ



በደንብ የተበጠረ አኩሪ አተር

- ከተወቃ በኃላ ፍሬውን ከገለባው መለየት፣
- ባዕድ አካላትን (ጠጠርና አፈር) ማስወገድ፤
- ደጋግሞ በማበጠር፡-
  - የአረምና የሌሎች ሰብል ዘሮችን፣ በተባይና በሽታ የተጎዱ፤ የተሰባበሩና የተጨማደዱ ዘሮችን መለየት፤
  - ዘሩን ከ95% በላይ ንፁሕ ማድረግ፤
- በደንብ ያልተበጠረ ዘር
  - ቶሎ አይደርቅም፣
  - ጥራቱ ስለሚቀንስ በገበያ ተፈላጊ አይሆንም፤

# 14 ማዳበሪያ/ጆንያ አመራረጥና አያያዝ



- የአኩሪ አተር ፍሬ በተባይ በቀላሉ የማይጠቃ ስለሆነ በማንኛውም ዓይነት መያዣ ማከማቸት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ማዳበሪያው ንጹህ፣ ያልተቀደደ እና በኬሚካል ያልተበከለ መሆን አለበት፡፡
- የተበጠረውን ዘር በ50 ወይም በ100 ኪሎግራም መጠን መቋጠር፡፡

# 15 ማጓጓዝ



- ሲጫንና ሲወርድ ማዳበሪያው/ጆንያው እንዳይቀደድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ
- የማጓጓዣ መሳሪያው (የመኪናው/ጋሪው ወለልና ግርግዳ የሚቧጭር ሹል ነገር የሌለበት፣ ዘይት ነክ ነገሮች ወይንም በፀረ-ተባይ መርዝ ያልተበከለ መሆን አለበት፡፡

# 16 ክምችት



- ከክምችት በፊት የዘሩ የእርጥበት መጠን ከ11-12% መድረሱን ማረጋገጥ፤
- ንፁሕና እርጥበት በማያገኘው ደረቅ ቦታ ላይ ማከማቸት
- በክምችት ወቅት ተባይ፣ ወፍ፣ አይጥ እንዳይበላው ጥበቃና ክትትል ማድረግ፤
- ከአንድ በላይ ዝርያ በአንድ መጋዘን ውስጥ የሚከማች ከሆነ ቦታቸውን መለየት፤
- የዝርያውን ስም፣ የተመረተበትን ዓ.ም እና ክብደቱን በጆንያው ላይ መጻፍ ያስፈልጋል::
- ክብደቱ ከ100 ኪሎ ግራም መብለጥ የለበትም::
- በክምችት ጊዜ ጆንያው አፈር እንዳይነካው ከሥር ሸራ/ኬንዳ ማንጠፍ::
- ድርድሩ ከጣሪያው አንድ ሜትር ዝቅ ማለት እና በሁለት ድርድሮች መካከል ከአንድ እስከ ሁለት ሜትር ርቀት ሊኖረው ይገባል::

# ከአኩሪ አተር የተዘጋጁ ምግቦችን መመገብ የሚሰጠው ጥቅም



ከአኩሪ አተር የተዘጋጁ የተለያዩ ምግቦች

አኩሪ አተር የምግብና ቅባት (ዘይት) ሰብል በመሆኑ በፕሮቲን፣ ቅባት እና ሌሎች አልሚ ምግቦች የበለፀገ ነው፡፡ ስለዚህ አኩሪ አተርን ከማሽላ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍና ሌሎች ሰብሎች ጋር ቀላቅሎ መመገብ ለጤንነት ጠቃሚ ነው፡፡ ከአኩሪ አተር በርካታ የምግብ ዓይነት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ:-

- ጥብስ፣ ፍርፍር፣ ሳምቡሳ፣ ቦምቦሊኖ፣ ብስኩት፣ ቂጣ፣ የቂጣ ፍርፍር፣ ዳቦ፣ አምባሻ፣ ቆሎ እና ዳቦቆሎ
- ወተት፣ አይብ፣ እርጎ፣ ማዮኔዝ፣ ሶስ/ድልህ፣ ወጥ እና ሌሎች ምግቦች ሊዘጋጁ ይችላሉ::

ለበለጠ መረጃ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስትቲዩት ያዘጋጀውን የአኩሪ አተር የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ይመልከቱ::

አኩሪ አተርን በማምረት:-

- ገቢዎትን ያሳድጉ
- የአፈር ለምነትን ያሻሽሉ
- የምግብ ዋስትናን ያረጋግጡ
- ጤናዎን ይጠብቁ

BENEFIT
Bilateral Ethiopian-Netherlands Effort for Food, Income and Trade

SBN

# የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ

ይህ የአኩሪ አተር አመራረት መመሪያ የተዘጋጀው በኒዘርላንድስ መንግስት በሚደገፈው የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራም ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የድጋፍ ፕሮግራምን (Benefit-SBN) ያነጋግሩ፡፡


## አድራሻ፡-

ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል
ፖ. ሣ. ቁ 1337
ቀበሌ 16
ስ.ቁ: +251 588119080/81
ፋክስ: +251 581120734
ጎንደር ኢትዮጵያ


WAGENINGEN UR
For quality of life





